# አገሬ ተጎዳች!

ታሪክ የነበራት ጥበብ ያልጎደላት፣
የተፈጥሮ ፀጋ ቸርነት ያልራቃት. . .፣
ለወግ ያልተመቸ አጉል ጊዜ ገጥሟት፣
አገሬ ተጎዳች! ወይ መዐት! ወይ መዐት!

ከገባችበት ማጥ ጎትቶ አውጥቶ፣
ፀዐዳ አልብሶ እሚቀባት ሽቶ፤
ዘንበል ካለችበት ደግፎ አቅንቶ፣
ንጹህ ውሃ እሚያጠጣት አርሞ. . ኮትኩቶ..፣
ቢሞከር . . . ቢቀመር. . . ጠብ ሳይል ከቶ፣
አገሬ ተጎዳች! ሁነኛ ሰው ጠፍቶ።
«ሰው» ማለት፣ «ሰው» ማለት . . .
«ሰው» ሊሆን የሚችል «ሰው» ያልተገኘ ዕለት!*1

ቀና እንደ ሙሴ*2 መንገድ እሚመራ፣
ንጹህ እንደ ራሄል*3 እንባ እምታዘራ፣
ብልህ እንደ ነብይ*4 ሕዝቦቹን እሚያሸሽ፣
ለመከራ ጊዜ ለፅልመት ቀን ሳይመሽ፣
ታጣና ባለሙ እነሆ እስከዛሬ፣
ተጎዳች በብርቱ ኢትዮጵያ አገሬ።

ጌታቸው አበራ
ታህሣሥ ፪ ሺ ፩ ዓ/ም
(ዲሴምበር 2009)

---

*1 የ«ሰው» ማለትን ሃሳብ የተዋስኩት - ከአበ-ተውኔት ዮፍታሄ ንጉሴ እና ከፈላስፋው ዲዮጋን ነው።

*2&3 የራሄል እንባ እና ሙሴ - የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ናቸው።

*4 ነብዩ መሐመድ - ወገኖቻቸውን ከእልቂት ለማዳን ወደ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ የመከሩትን ታሪክ በማስታወስ።